አንዳችሁ ወንድሙን ያገኘ ጊዜ በርሱ ላይ ሰላምታን ያቅርብ! በመካከላቸው ዛፍ ወይም ግድግዳ ወይም ድንጋይ ከጋረዳቸው ከዚያም ድጋሚ ቢያገኘው በድጋሚ በርሱ ላይ ሰላምታን ያቅርብ።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ
ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል፦ "አንዳችሁ ወንድሙን ያገኘ ጊዜ በርሱ ላይ ሰላምታን
ያቅርብ! በመካከላቸው ዛፍ ወይም ግድግዳ ወይም ድንጋይ ከጋረዳቸው በኃላም ድጋሚ ቢያገኘው በድጋሚ በርሱ ላይ ሰላምታን ያቅርብ።"
[ሶሒሕ ነው።] [አቡዳውድ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ሙስሊም ሙስሊም ወንድሙን ባገኘው ጊዜ በርሱ ላይ ሰላምታን ማቅረብ እንደሚገባ አነሳሱ። አንድ ላይ እየተጓዙ እንኳ በመካከላቸው እንደዛፍ ወይም ግድግዳ ወይም ትልቅ ድንጋይ ከለያያቸው በኋላ በድጋሚ ቢያገኘው በርሱ ላይ ሰላምታን እንዲያቀርብ አነሳሱ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/3552